የከተማችንና የክልላችን መስተዳደሮች በውድባፋሎ ክልል ዙሪያ ያሉ ነዋሪዎች የቧንቧ ውሃን አፍልተው እንዲጠቀሙ መክረዋል። ውሃ ከፈላ በኋላ ለአንድ ደቂቃ የሚያህል ጊዜ ሊፍለቀለቅ ይገባል።

ህጻናት ቤት ወስጥ ካሉ የውሃ ማፈያ ማንቆርቆሪያውን ከኋላ በኩል ካሉት የስቶቭ ምድጃዎች ላይ ይጣዱት። ይህንን ማድረግዎ ህጻናት እንዳይቃጠሉ ይከላከላል። ያለምንም ማፋሰስ ከውሃ ማፈያው ማንቆርቆሪያ ጋር ሊያነሱ የሚችሉትን የውሃ መጠን ብቻ ያፍሉ። ከቀናት በፊት የተሰሩ በረዶዎችን በማስወገድ የበረዶ መስሪያ ትሪውን ከጀርም ነጻ እንዲሆን አድርገው ይጠቡ። የፈላውን ውሃ በማቀዝቀዝ በረዶ ይስሩ።

**ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ነገሮች ውሃ አፍልተው ይጠቀሙ፡-**

ለመጠጣት
ምግብ ለማብሰል
የህጻንትን ፎርሙላ ለመስራት
በረዶ ለመስራት
አትክልትና ፍራፍሬዎችን ለማጠብ
ጥርስ ለመቦረሽ
የቤት እንስሳትን ለማጠጣት

በቧንቧ ውሃ ሰውነትን መታጠብ የጤና ጉዳት አያስከትልም